# ምንም የፖሊሲ ስምምነት በሌለበት የኦሮምኛ ቋንቋ ተማሩ ብሎ ማወጅ ሕገ-ወጥ ነው።

September 26, 2018

የቋንቋ ጉዳይ
***
መላኩ አዳል
***
ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በኦሕዴድ 9ኛ ጉባኤ ላይ ግሩም ንግግር አድርገዋል። ኦሮሞ አይገነጠልም፣ የኢትዮጵያ ብሎም የአፍሪካ እድገት ዋና አጋር ይሆናል ብለዋል። የኦሮሞፓርቲዎችም ለኦሮሞውም ለኢትዮጵያም ታማኝ እንዲሆኑ መክረዋል። ይህም እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ደስ ብሎኛል። ምንም እንኳን የአዲስ አበባ ወጣትን ያለ ምንም ምክንያት ማሰራቸው፣መፈንቅለ-
መንግስት ተሞከለበት ወሬ እና የኦነግ አባላት የሚያደረጓቸው ነገሮች ሁሉ ለአገራችን ህልውና ግልፅ ተግዳሮት ቢሆኑም።

ነገር ግን ኦሕዴድ/ኢሕአዴግ የኦነግን የኦሮምኛ ጽሑፍ በግዕዝ ፊደላት ሳይሆን በላቲን ፊደላት ይሁን የሚል ጥያቄ የራሱ በማድረግ እንዲፈፀም አድርጓል። በዚህም የብዙ ኦሮሞ ወገኖቻችንየሥራና የቦታ ምርጫ ተወስኗል። አሁን ደግሞ ኦሮምኛ የፌደራል ቋንቋ እንዲሆን እየተጠየቀ ነው። ሌሎችንም ቋንቋዎች ባካተተ መልኩ ሕገ-
መንግሥት ተሻሽሎ መሆን ይችላል። የቋንቋወጥነትን መጠበቅና ብዙ ቋንቋዎችን መቻል ወጥ የሆነ ፖለቲካ-ኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ለመፍጠርም እንደሚያግዝ አምናለሁ።

የትምህርት ስርዓቱን ለማሻሻል ፍኖተ-
ካርታ መሰራቱንና ውይይት እየተደረገበት መሆኑን እናውቃለን። አሁን ደግሞ የአዲስ አበባ ልጆች ኦሮምኛ እንዲማሩ መወሰኑን እየሰማን ነው። ይህ የቋንቋተማሩ ውሳኔ የትምህርት ሥርዓት ለውጡን የሚያውክ ነው። በተጨማሪም የኔ ጥያቄ ይህ የቋንቋ ዜና የግዛት ማስፋፋት ወይስ ኦሮማዜሽን? ልጆቻችን ኦሮምኛ ሚማሩትና የፌዴራል ቋንቋየሚሆነው የላቲን ጽሑፉን ይዞ ወይስ የግዕዝ ፊደላትን ሲጠቀም?

ምንም የፖሊሲ ስምምነት በሌለበት የኦሮምኛ ቋንቋ ተማሩ ብሎ ማወጅ ሕገ-ወጥ ነው።

መላኩ አዳል